**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**
**የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**

**በሰኔ ወር 2000 ዓ.ም በተቀዋሚዎች ቀን በኢዴአፓ-መድህን ፓርቲ በኩል በሀገራችን የተከሰተውን የድርቅ ሁኔታ አስመልክቶ የቀረበ የመወያያ አጀንዳ**

ላለፉት አርባ ዓመታት ሀገራችን ኢትዮጵያን ተደጋጋሚ የድርቅ አደጋ ያጋጠማት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም ድርቅ ምክንያት በርካታ ዜጎች ለዘመናት ያጠራቀሙትን ጥሪት አሟጠዋል፤ ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለዋል፤ ተሰደዋል፤ ህይወታቸውንም አጥተዋል፡፡

ባለፉት ወራት ወቅቱን የጠበቀ ዝናብ ባለመጣሉ በገጠር የሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት በተከሰተው ድርቅ በእንስሳትና በሰዎች ላይ የርሀብና የሞት አደጋ የደረሰ ሲሆን፤ በከተሞች አካባቢ ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት የዜጎችን የመኖርና ያለመኖር ህልውና እየተፈታተነ መሆኑ ይስተዋላል፡፡

ከጉዳዩ አሳሳቢነት አኳያ በቂ ነው ባይባልም በመንግሥት በኩል በጉዳዩ ላይ መግለጫ እየተሰጠ ሲሆን፤ አንዳንድ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኀንም ይህንኑ የድርቅ አደጋ ከህጻናት የምግብ እጥረት (Malnutrition) ጋር አያይዘው የተጎጂዎቹን ቁጥር እየጠቀሱና ምስላቸውን እያሳዩ በመዘገብ ላይ ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኀን አማካይነት የታዩት በርሀብ የተጎሳቆሉና የተጎዱ ዜጎች ምስል፤ የደረሰውን ድርቅና ርሀብ አስከፊነት ብቻ ሳይሆን፣ ችግሩ ሳይነገር ለበርካታ ወራት የቆየ መሆኑንም ያስገነዘበ በመሆኑ፤ «ይህ ሁሉ ጉዳት እየደረሰ መንግስት ጉዳዩን ሳይገልጽ ለምን ዘገየ?» የሚል ጥያቄ እንድናነሳ አድርጎናል፡፡

ይህም ሆኖ፤ መንግስት የኢኮኖሚ ሁኔታውን ለማረጋጋት ከድጎማ ጀምሮ ልዩ ልዩ የማስተካከያ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን በበጎነት የምናየው ይሆናል፡፡ ከችግሩ ስፋትና ውስብስብነት አኳያ በአጭር ጊዜ መፍትሄ ሊያበጅለት እንደማይችልም እንረዳለን፡፡ በተበጣጠሰ ማሳ ላይ የተመሰረተና የዝናብ ጥገኛ የሆነ የግብርና ፖሊሲ መከተል ከልመና ሊያወጣ እንደማይችልና እንዲህ ዓይነት አጣብቂኝ የሆነ ህልውናን የሚፈታተን ሁኔታ እንደሚያስከትል ደጋግመን የገለጽነው ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ፤ ይህ አሳሳቢ ሀገራዊ ችግር በየትኛው የሀገሪቱ አካባቢ እንደተከሰተ፣ የችግሩ መጠን ምን ያህል እንደሆነ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ምን ያህል እንደሆኑ፣ እስከ አሁን ድረስ አደጋውን በመከላከል ረገድ የተወሰደው እርምጃና ወደፊት በሚከናወነው ቀጣይ ሥራ የመንግሥት፣ የህዝቡና የዓለም አቀፍ ለጋሾች ድርሻ ምን እንደሆነ የተገለጸ ነገር ባለመኖሩ ጉዳዩን አሳሳቢ አድርጎታል፡፡

ስለሆነም፤ የተከበረው ምክር ቤት ተወያይቶ የጋራ ግንዛቤ እንዲይዝበትና የተከበሩ የምክር ቤት አባላት ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ጀምሮ ወደየተመረጡበት አካባቢ በሚሄዱበት ወቅት ከመረጣቸው ህዝብ ጋር በመመካከር ችግሩን በመከላከል ረገድ አስፈላጊውን ለመፈጸም እንዲችሉ ይረዳል በማለት ይህንን አጀንዳ ለውይይት አቅርበናል፡፡